# ኪዳነ ምሕረት፦

እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ካለው ግንኙነት አንዱ «ቃል ኪዳን»ነው። ዓለሙን ከፈጠረ በኋላ የሚመግበው በዚሁ በቃል ኪዳን ግንኙነት ነው። ከዚህም በላይ ከሰው ልጆች ጋር ካሉት ልዩ ግንኙነቶች አንዱ ቃል ኪዳን ነው።

«ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ፦ ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ»(መዝ.፹፰፥፫) ብሎ እንደተናገረ ከብዙዎቹ ጋር ቃል ኪዳን አለው። ምድርን ዳግመኛ በንፍር ውኃ ላይመታ ፤ ሥጋ ለባሸንም አንድ ጊዜ ፈጽሞ ላያጠፋ ለኖኅ ቃል ኪዳን ገብቶለታል።(ዘፍ.፱፥፩-፲፯)የምድር አህዛብም በዘሩ እንዲባረኩ ለአብርሃም ቃል ኪዳን ገብቶለታል (ዘፍ.፳፪፥፲፰) ለይስሐቅና ለያዕቆብም ተስፋቸውን ነግሯቸዋል።(ዘፍ.፳፮፥፬) ለቅዱስ ዳዊትም ምሎለታል።(መዝ.፹፰፥፫) የእነዚህ ሁሉ ቅዱሳን ኪዳን ፍጻሜ ያገኘው ግን በአምላክ ሰው መሆን ነው።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ክርስቲያኖች በእርሱ ለሚያገኙት ፀጋ በረከትና ሀብት መንገድ አድርጎ ካስቀመጣቸው ውስጥ አሁንም ኪዳን ዋናው ነው። ለዚህም በዘመን ሥጋዌው «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ፤ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ፤ ፃድቅንም በፃድቅ ስም የሚቀበል የፃድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።» ሲል ያስተማረውን ማስታወስ በቂ ሊሆን ይችላል።(ማቴ.፲፥፵-፵፪)

በየቅዱሳኑ ገድላት ላይ እንደምንመለከተው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእነርሱ የሚገባውን ኪዳን ነው። ይህ ቃል ኪዳን የገድላቱ አንዱ ክፍል ከመሆኑም በላይ የቅዱሳኑ የዕረፍት መታሰቢያ(በዓል) እንዲከበር አንድ መነሻ ሆኖ ያገለግላል። ስለዚህም እግዚአብሔር በወዳጆቹ አድሮ ለሕዝቡ የሚያደርሰው የምሕረቱ መገለጫ በመሆኑ በቅዱሳኑ በዓላት ይነገራል ፤ ትምሕርት ይሰጥበታል ፤ አማኞችም አምነው በቃል ኪዳናቸው እግዚአብሔርን በመማፀን ይጠቀሙበታል።

የእመቤታችን ቃል ኪዳን ለየት ያለ ነው።ለየት የሚለውም በሁለት ዐበይት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው እርሷ ምልዕተ ፀጋ በመሆኗና ፍጽምት ርህርሀተ ሕሊና ከመሆንዋ የተነሣ ስለ ሰው ልጆች አብዝታ የማለደች እናት እና ክርስቲያኖች ሁሉ ይድኑ ዘንድ ከሌሎቹ በተለየ የለመነች በመሆንዋ ነው።እንኳን እግዚአብሔር ጨካኙ ዳኛ እንኳን አብዝታ ለለመነችው መበለት ያደረገውን እናውቃለንና።(ሉቃ. ፲፰፥፩-፰)

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ወላዲተ አምላክ ለመባል የበቃች ከእርስዋ በቀር ሌላ የሌለ ፤ በዚህም መልዕልተ ፍጡራን ትሆን ዘንድ አምላክ ያከበራት በመሆንዋ ልዩ ቃል ኪዳን ይገባላት ዘንድ የተገባት ናት። ለአምላክ እናትነት(ልዩ) ሆና መመረጧን ለሚያምን ሁሉ ልዩ ቃል ኪዳን መቀበሏ ጥያቄ አይሆንበትም። ስለዚህም ልዩ ቃል ኪዳን ተገብቶላታል። ነቢዩ ኢሳይያስ ወይወጽእ እምጽዮን መድኅን ወየዐትት ኃጢአተ እም ያዕቆብ ወዛቲ ይእቲ ኪዳኖሙ እንተ እምኀቤየ ይቤ እግዚአብሔር፦ መድኅን (ክርስቶስ) ከጽዮን ይወጣል (ከእመቤታችን ይወለዳል) ፣ ኃጢአትንም ከያዕቆብ (ከእስራኤል ዘነፍስ) ያርቃል ፤ ለእስራኤል የማልሁላቸው መሐላ የገባሁላቸው ቃል ኪዳንም ይህቺ ናት ፤ ሲል እንደተናገረ እግዚአብሔር ልዩ ውልና ስምምነት ከእስራኤል ዘነፍስ ጋር አለው።(ኢሳ.፶፱፥፳-፳፩) ከዚህ ውስጥ አንዱና ዋናው ከእመቤታችን ጋር ያደረገው ነው።

ይህ ኪዳን ልዩ ከሆነበት ነገሩ አንዱ የራሱ መታሰቢያ ዕለት ያለው መሆኑ ነው። ዕለቱም ጌታችን በጌቴሴማኒ ተገልጾ ኪዳኑን የገባበት ዕለት ነው ፤ ይኸውም የካቲት ፲፮ ቀን ነው። እመቤታችን ከላይ እንደተገለጸው ወደ ጎልጎታ ወደ ጌታ መቃብር እየሄደች አብዝታ ትለምን ነበር። በዚህም ምክንያት መላእክት ወደ ሰማያት አሳርገው ገነትንና ሲዖልን አስጎብኝተዋታል። እርስዋም በሲዖል ያሉ ነፍሳትን አይታ በእጅጉ አዝናላቸዋለች ፤ ከዚህም በኋላ ስለ ኃጥአን አብዝታ ስትለምን ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚች ዕለት ተገልጾ ልዩ የምሕረት ቃል ኪዳን ስለገባላት ኪዳነ ምሕረት እየተባለች ትከበራለች። ይልቁንም ከላይ የገለጽነው በኢሳይያስ አድሮ የተናገረው የኪዳን ቃል እመቤታችንን ያስታውሳል። «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ» የሚለውን ለአዳም የገባውን ኪዳን የፈጸመው በእመቤታችን ስለሆነ እርስዋ እራስዋም ኪዳነ ምሕረት እየተባለች ትጠራለች። ማዳኑን የፈጸመባት በኋላም ተነሳሕያን ኃጥአን ይቅርታን ያገኙ ዘንድ ኪዳን የገባላት ናትና። ስንክሳሩም በመግቢያው ላይ «በዚችም ዕለት የክርስቲያን ወገኖች ሁሉም አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዓልን ያደርጋሉ። በዚች ዕለት መታሰቢያዋን ለሚያደርግ ስሟን ለሚጠራ ለድሆችና ለችግረኞች እስከ ቀዝቃዛ ውኃ ለሚሰጥ

የክብር ባለቤት ከሆነ ከተወደደ ልጅዋ ከጌታችን ከአምላካችንና ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምሕረት ቃል ኪዳንን /ኪዳነ ምሕረት/ተቀብላለች» ይላል(ስንክሳር የካቲት ፲፮ ቀን)። ጌታም ይህን ቃል ኪዳን በነሐሴ ፲፮ ቀን ደግሞታል።

እኛም ከዚህ እጅግ ሊያስተውሉት ከሚገባ ታላቅ መልእክት የምናገኘው ትልቅና ታላቅ ቁም ነገር እግዚአብሔር ከመረጣቸውና ካከበራቸው ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ ሲሆን አብዝተው ለጠየቁትና ለተማጸኑት የቅርብ አምላክ እንጂ የሩቅ አምላክ አለመሆኑን ማሳየቱና ጸሎታቸውንና ልመናቸውን ሰምቶ ምላሽ መስጠቱን ነው። ስለሆነም አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ከገባላት የመስቀል ሰጦታ እናታችን በረከትን ለማግኘት ዘወትር በተሰበረ ልብና በተዋረደ መንፈስ መቅረብ ያስፈልጋል። ነቢዩ ኤርምያስ «አቤቱ የሆነብንን አስብ» ብሎ እንደጮኸው ጩኸት እያንዳንዳችን የምሕረት ቃል ኪዳንን ወደተቀበለች ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንቅረብ። ልዑል እግዚአብሔር ንጉሥ ሰሎሞንን ስለ አባትህ ስለ ዳዊት ስል በትረ ንግሥናህን ከአንተ አልወስድም ብሎ ቃል እንደገባለት እኛም የዘላለም ቃል ኪዳን ስለገባላት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ሲል እንዲምረን ፍጹም ትህትናን ገንዘብ አድርገን እግዚአብሔር ያከበራቸውን አክብረን መገኘት ይኖርብናል። በዚህ ታላቅ ፆምም በረከትን ለማግኘት ፆማችንን ከግብር ጋር አገናኝተነው ደካሞች የሚረዱበትን ፣ ታማሚዎች የሚጠየቁበትን ፣ እስረኞች የሚጎበኙበትን ፣ የታረዙ የሚለብሱበትን ፣ የተራቡ የሚጠግቡበትን ፣ የተጠሙ የሚጠጡበትን መንገድ ለማመቻቸት የተዘጋጀን መሆን ይኖርብናል። ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው ብሎ ሐዋርያው ያዕቆብ እንደተናገረ እኛም ፆምንና ምፅዋትን አስማምተን ለበጎ ሥራ የተዘጋጀን እንድንሆን አምላካችን በቸርነቱ ይርዳን ፤ እመቤታችን በተገባላት ቃል ኪዳን ትጠብቀን።

## ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር


**በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በሰሜን አሜሪካ**
**የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ትምህርት ክፍል።**